# ተቃዋሚ ጋዜጣ ባለቤቶች ገመና ከውስጥ አዋቂ የተሰጠኝ ሰነድ
## ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ)



በርዕሱ ላይ ተቃዋሚ ጋዜጠኞች..... በሚለው ምትክ ‘የነፃ ጋዜጣ ባለቤቶች...’ በሚል ቃል ልጠቀም አስቤ ነገር፤ ሆኖም ካንዳንዶቹ በቀር፤ ብዙዎቹ የመጻፍ/የንግግር ነጻነት አክባሪዎች ስላልሆኑ እንዲያም ሆኖው በተቃወሚ ጎራ ስለሚገኙ ‘ተቃዋሚ ጋዜጣ ባለቤቶች” የሚለውን መርጫለሁ። በቅርቡ ስለ አብይ አሕመድ በሚመለከት በጠባብነታቸው የታወቁ “ኒሂሊስት/አገር አፍራሾች” የኦሮሞ ሊሂቃን አብይ አሕመድ በሰጠው ኢትዮጵያዊነት ንግግር ቅር ተሰኝተው “ዝቅተኛ ነጥብ” ሰጥተነዋል፤ ብለው ሲወሻክቱ አድምጬአቸው፤ ለነዚህ “የሜንጫ አብዮቶኞች” መልስ ሰጥቼአቸው ነበር። (**All the Machete Group are Having a Twitch ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ)** ይህ ትችት በአንዳንድ ድረገጾች ሲለጠፍ በዘሐበሻ አልወጣም። የኦሮሞ ንህሊስቶች ሲተቹ ዘ-ሐበሻ አዘጋጅ ለምን እንደማይመቸው ለኔ እንቆቅልሽ ነው። የተቃዋሚ ጋዜጦች/ድረገጾች/ የሚላኩላቸው ጹሑፎች የማተም ያለማሳተም መብታቸው የተጠበቀ ቢሆንም፤ ያልወደዱት ምክንያት ካለ ሲጠየቁ፤ “መልስ” ከመስጠት ይልቅ ይሸሻሉ። ይህ ሽሽት ደግሞ የሚያሳየው አሳማኝ ሆኖ ሳያገኙት ሲቀር ለራሳቸው አምነው የመተቸት ነጻነትን በማፈኑ ባህሪ ይቀጥላሉ።

ይህ ብዙ ጉዜ የተቸሁበት ነው። ተቃዋሚው እጅግ አደገኛ አፋኝ እንደሚሆን ካሁኑ የምናየው ባህሪው ምልክት ነጋሪ እንደሆነ እርግጠኛ ሆኜ ለመከራከር እችላለሁ። የሚተቹት ድርጅቶች/ግለሰቦች ካሉ እነሱ መልስ እንዲሰጡበት ከማድረግ ይልቅ ‘እነሱ ሳይወክሉዋቸው ተወክለው ተቺዎቻቸውን ያፍነናሉ”። ካሁን በፊት እኔን የተቹ የኢሕፓ ማሞ ቂሎች እኔን ለመተቸት እኔ በአምደኛነት የምገኝባቸው ድረገጸች ሲልኩ ‘ይለጥፉላቸዋል”። እኔም መልስ እሰጣለሁ። እኩል ያገለግሉናል። ዘ-ሐበሻ ግን እጅግ ለየት ይላል። ባጭር ቃል፤ ኦነጎች እና ኦነግ መሳይ ብጥቅጣቂ ድርጅቶችን “የሚተቹ ጽሁፎች ስልክለት” ግን አይወደውም። ያፍናቸዋል። ማፈን ለወያኔም አልጠቀማትም። ወንድሞቼ የሰውን ንግግር ከማፈን የባሰ መራራ ነገር የለም። ከዚያ ብልግና ባህሪ እራሳችሁን አጽዱ።

የኔ ጽሑፍ አፋኞቹ ፈለጉም አልፈለጉም ሰው ፈልጎ ፈላልጎ ያነባቸዋል፡ (የሚላኩልኝ መልእክቶች ነጋሪዎች ናቸው) ብዙ አድናቂና ተከታይ አፍርቻለሁ። ብዙጠላትም አፍርቻለሁ። ኢትዮጵያን በጠላትንት የከበብዋት ሁሉ እኔንም እንደስዋ ከብበውኛል። የሚጠልዋት ሁሉ እኔም ስለምጠላቸው እኔንም እስዋንም እኩል በማይምር ጨካኝ ቢላዎቻቸው መክተውናል። የድረገጽ ባለቤቶች ጠላታቸው ውሱን ነው፡ “ወያኔ’ ብቻ ነው። ከዚያ በላይ ያሉት እኛ ተቺዎች የምንጋፈጣቸው ቡድኖች/ግለሰቦች በጣላትነት

አይመለከትዋቸውም። እኛ ከነሱ የበለጡ ጠላቶች አሉን። ባብዛኛው በድረገጽ ባለቤቶቸ በኩል የሚልኩትን እየለጠፉላቸው እኛን ያስጠቁናል። መልስ ለመስጥም እንታፈናለን። የኛ ሲሆን አያትሙትም። ስለዚህ ከድረገጾችም ከፖለቲከኞችም ካፍራሽ ሃይሎችም የሚሰነዘርብን ጠላትነት በኛ ላይ ሲያርፍ ብዛቱ የት የሌለ ነው። ሌላ ቀርቶ በነጃዋርም ሆነ ያ የወያኔ፤ የሻዕቢያና የኦነግ ሎሌ ህዝብ ለማጋደል የተቀጠረ ወንጀለኛው ተስፋየ ገብረአብ፤ መልስ ስንሰጠው "የናን እያፈኑ" እሱን እሽሩሩ እያሉ ከሱ ጋር አብረው ሲያቦኩ፤ በየቀኑ እየጋበዙ አናካሽ ጹሑፎቹን እየለጠፉ ሲያስሰድቡን የነበሩት እነዚህ ተቃዋሚ ነን የሚሉ ድረገጾች መሆናቸው ሰነዶቹ አሁንም ተዘግበው አሉ።

የማታ የማታ (አት ዘ ኢንድ ኦፍ ዘ ደይ) ቀን መሽቶ ጀምበርዋ ስትወጣ ፤ የድረገጽ ባለቤቶች አፈና ባጭር ሲቀጭ፤ስርዓት ሲለዋወጥ፤ዘመን ሲለወጥ፤ የኔ መጻህፍቶች ከትውልድ ትውልድ ተሻግረው እኔን ከመቃብር በላይ ዝንተዓለም እንድኖር ያደርጉኛል። ይብላኝ የምልላቸው ግን አንባቢ በብዛት ለማግኘት ሲሉ "ሙላሆቹ ፤ ሙጃሃዲኖች እና የቁቤ ፈላስፋ አሚሮችን" አሳፋሪ የቅኝ ግዛት ምንጣፍ አንጣፊ አነጎችና ሻዕቢያዎችን ሁሉ እያገለገሉ የኢትዮጵያን አንባቢ ሕሊና (ሰቨርዝርን) በመበከል ከፍተኛ ጉዳት (ዳመጅ) የሚያደርሱ በድረገጽ ጎብኚዎቻቸው ገንዘብ የሚሰሩ እንጂ እኔ እና መጽሐፍቶቼ ለዘላለም በየዜጎች ቤት እና መጽሐፍተ ቤቶች በክብር እንኖራለን።

ስለ ተቃዋሚ ድረገጾች እና የጋዜጣ የመጽሔት ባለቤቶች በዝባዥና የነጻ ሃሳብ አፋኝ ባሕሪ ሳስብ አንድ ወዳጄ የላከልኝ ሰነድ ካስቀመጥኩዋቸው ማህደሮች አውጥቼ ስፈትሻቸው፤ እዛ አገር ውስጥ እያሉ ሲያደርጉት ነበረው ባህሪ እዚህ አውጭ አገርም ከመጡት መካከል ዛሬ የድረገጽ ባለቤቶች የሆኑት ባህሪ እንድፈትሽ ተገደድኩ። እና ወዳጄ በሰነዱ ላይ ያጫወተኝን ላካፍላችሁ። አስቀድሜ ተገቢውን ምስጋና ለወዳጄ ለመስጠት እፈልጋለሁ፡ አመሰግናለሁ።

<" ኢትዮጵያ ውስጥ አሁንም የአሉና የነበሩ ጋዜጣ ባለቤቶች/አሳታሚዎች ዘጠና አምስት ከመቶ ያክሉ ከፍተኛ የሆነ የአዕምሮ ብዝበዛ ያካሂዳሉ።እነዚህ አሳታሚዎች በየሰምንቱ ከሚሸጡ ጋዜጦች በሳምንት በ10ሺሕ ብር የሚቆጠር ገንዘብ ገቢ ያገኛሉ። ደም ተፍቶ አዕምሮውን አስጨንቆ እራሱን እና ቤተሰቦቹን ለአደጋ አጋልጦ ለሚሰራው ጋዜጠኛ ግን 50 ብር ይወረውሩለታል፡ (ልብ በል ጌቾ ሐምሳ ብር ነው"!)። ደህና ክፍያ ይከፍላሉ የሚባሉት አሳታሚዎች ጣሪያው 200 ብር።ከሪፖርተር ጋዜጣ ጀምሮ ይህንን ነው ሚያደርጉት። እነ ሺመልስ ከማልን፤ እኔን ጨምሮ ሪፖርተር ጋዜጣ የሚከፍለን ትልቁ 800 ዝቅተኛው ደሞዝ 200 ነበር። የዛ ጊዜ ጋዜጣው ከ80 ሺሕ እስከ 90ሺሕ ያስገኝ ነበር።

ሌሎች ደግሞ 20 ብር የሚከፍሉ ነበሩ። አሜሪካ የገባ አንድ የጋዜጣ አዘጋጅ በሳምንት 20 ብር በወር 80 ብር ይከፈለው እንደነበር አውቃለሁ።የጋጣ ባለቤቶች በሚጽፉዋቸው ርዕሰ አንቀጾች ላይ ስለወያኔ ኢ-ፍትሐዊ አስተዳደር፤ስለ ማሕበረሰቡ ኢኮኖሚያዊ ችግር፤ ስለ የኑሮ ውድነት እና ስለማይመጥናቸው ደሞዝ እየጻፉ ወዘተ... ብዙ ብዙ ይላሉ። እነሱ ግን ከወያኔ በባሰ ስግብግነት ተዘፍቀው ይምቦጫረቃሉ።

በ1995/1996 ስለፕሬስ በሚመለከት ግዮን ሆቴል ስብሰባ ተጠርቶ በረከት ስሞኦን የተናገረው አስታውሳለሁ። <”የጋዜጣ ባለቤቶች በየሳምንቱ በ10ሺ የሚቆጠር ገቢ እያገባችሁ ለጋዜጠኞቻችሁ ግን 50 ብር እና 20 ብር እንደምትወረውሩላቸው እናውቃለን።”> ብሎ ነበር። በወቅቱ በርካታ ጋዜጠኞች ቁስል ነበር የነካው።ነገር ግን እነ በረከትን አምኖ አቋም መውሰድ ስለማይቻል ጋዜጠኛው ዝምታን መረጠ።በሌላ በኩል ጋዜጣ አከፋፋዮች እንኳ የሚያገኙት ገቢ የት የሌለ ነው። አራት ኪሉ የሚያከፋፍሉ ‘ፍቅሬ እና መርእድ’ ብቻ ለምሳሌ ልግለጽ። አንዱ በጉራጌ ክልል አንዱ ባዲስ አበባ ጋራዥ ቤት ገንብተዋል።ታክሲም አላቸው። ሌሎቹ ታክሲ የሌላቸው፤ቤት ያልገነቡ፤ትላልቅ መድብር አልከፈቱ አታገኝም።

ዋናው ጥየቄ፤ለምን አገኙ፤ለምን ተሻሻሉ አይደለም።ይህንን የሚጠይቅ ጤነኛነትን አያመለክትም። አሳታሚዎችም በሕግ ሠርተው ያገኙት ነው ። ግን ሁለቱም የገቡ ምንጭ ‘ጋዜጠኛው ነው”።እሱ ባይኖር ፤ባይዘግብ አሁን የደረሱበት ደረጃ ባልደረሱ ነበር። ልዩነቱ ግን የሰማይና የመሬት ሆኖ ፤ በፊት የነበረውም ሆነ አሁን ያለው ጋዜጠኛ አፈር ድሜ እንዲበላ ተፈርዶበታል። ባጭሩ ተቆርቋሪና አሳቢ በማጣት የሌሎች ሃብት ምንጭ ሆኖ እንዲአገለግል በጭምት ተፈርዶበታል። እኩል ተጠቃሚ ቢሆን ኖሮ ወደስደት የአመራውም ሆነ አገር ውስጥ ያለው ማንንም ሳያስቸግር ፤ የሰው ፊት ሳይገርፈው በራሱ ጌዜ ይንቀሳቀስ ነበር። ይህንን አውነት ብትናገር፤ የጋዜጣ ባለቤቶች ባንድነት እየተረባረቡ ፤ <”ወያኔ ሆነ፤ ለነ በረከት አደረ”> እያሉ ያወግዙሃል። አግረመንገዱ የራሳቸውን ገመና ለመሸፈን የሯሯጣሉ። ይሄ ደው የለውጥ ሓዋርያ (ጌቾ ፍረድ!)።

*ጌታቸው ወንድሜ ሌላ ዋቢ ልጥቀስልህ፤*

ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ሁሉም የነጻ ፕሬስ ጋዜጣ የሚያውቃቸውና በሚሠሩት የስነጽሑፍ (ጋዜጠኛነት) ስራ ተቀባይነትና አድናቆት ያገኙ ሁለት ጋዜጠኞች ልጥቀስ። ሰለሞን ሙሉታፈሰ ይባላል። በነገራቸን ላይ ስለ ሰለሞን ያ ወሽካታ ተስፋየ ገበረአብ መጽሐፉ ውስጥ ጠቅሶት ነበር (በአድናቆት)። ሌላው ጋዜጠኛ አለምሸት ሞገስ ነው። ኢሕአዴግ አጥብቆ የሚፈራው ነበር ሰለሞን ሙሉታፈሰ ጊዮርጊስ ቤ/ክ በረንዳ ጥግ ተኝቶ ያድር ነበር። ጤናው ተቃውሷል።አለምሸት ሞገስ ደግሞ ጥዋት በማለዳ በባዶ ሆዱ ካቲካላ እየጠጣ በደሮ ማነቅያ ተኝቶ ሲለፈልፍ ይውል ነበር። አሁን በምን ሁኔታ እንዳለ አለውቅም።እነዚህ ጋዜጠኞች 50 ብር ነበር ሲከፈላቸው የነበረው። በእነሱ ጫንቃ እና ብዕር የከበረ ግን ስንት እና ስንት የጋዜጣ በለቤት ነው።

ሌላው ጋዜጠኛ ፥ ኮሞዲያን ፥ የግጥም ደራሲ ፋሲል ተካልኝ ነው። አበባና ትዕግስት ለሚባሉ ዘፈኖች ግጥም እና ዜማ ሰጥቷል። እነኚህ ካሴቶች ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ ሲሸጡ ለእርሱ የሰጡት ግን አንድ ሺሕ ብር ከፍለውት ቀሪውን አንድ ሺሕ ከለከሉት። <“እርጅና አብሮ አደጌ”> የሚለው ዘፈን ገጣሚ ታደሰ ገለታ ይባላል። ሁለቱም አንስት

ዘፋኞች የታወቁት በዚህ ሲሆን፤ ለደራሲው ሳንቲም አልሰጡትም። ስንቱን ብየ ልዘርዝርልህ ጌታቸው እጅግ ብዙ በደል ነው የተሰራው። በሰፊው ሌላ ጊዜ አጫውታሃለሁ"> በማለት

ጋዜጠኛ ወዳጄ ስለ "ነጻ" ጋዜጣ ባለቤቶችና ከጋዜጠኞች ጋር ያለቸው ግንኙነት እንዲሁም ዘፋኞች ፥ ዜማና ግጥም ሰርተው ከሚሰጡዋቸው ጋር ያለው ብዙዎቻችን የማናውቀው ምስጡር አጫወቶኛል። እነዚህ ለነጻነትና ለመናገር መብት ቆመናል የሚሉን ወንድሞችና እህቶች "እንዲህ ያለ" የተደበቀ ገመና በዲቴክቲቭ ጋዜጠኞች በኩል ተጠንቶ ቢቀርብልን ብዙ ባወቅናቸው። ምናልባትም ይህ በር ከፋች ስለሚሆን የምታውቁትን ታሪክ እንድታካፍሉን እጋብዛለሁ። የምታውቀውን ፥ ያጠናኸውን፥ ያታዘብከውን የሰማኸውን ቅር ያለህን 'አትናገር ፥ አትጻፍ' ብሎ የሰውን አንደበት የሚያፍን ጋዜጠኛ እና የድረገጽ ባለቤት እጅግ አረመኔ ስለሆነ ከወያኔዎች እኩል መወገዝ ይገባዋል። አሁን በነፃነት አገር እውጭ አገር ተቀምጦ እንዲህ የለመደበት፤ አገር ነጻ ስትወጣ ፥ ተመለሱ ሲባል ፥ ወደ አገር ለመመለስ ወስኖ ዕድሉ ካገኘና የጋዜጣና የራዲዮ ባለቤት ቢሆን በመጪው ስርዓትም በከፋ መልኩ ያንን ባህሪይ እንደሚቀጥልበት በእርግጠኛነት ማመን ይቻላል። ለዚህ ነው ተቃዋሚው ድረገጽ ባለቤቶች ካሁኑ ከአፈና እና ከመደልዎ ባህሪ ራቁ የምንላቸው ለወደፊቱ እነሱም ሌሎች አፋኝ ወጣት ትውልዶች እንዳያፈሩ የምንመክረው። አድለዎ አትስሩ ፤ ከማፈን ይልቅ የምንተቻቸው ሰዎች ራሳቸው ይሞግቱን፤ እንናንተ እማሃከል አትግቡ ፥ አናግሩን አታፍኑን!

አመሰግናለሁ
ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ ብሎግ አዘጋጅ)።